# Building Bridges of Faith Against Domestic Violence

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህናት በኢትዮጵያ ለሚደርሰው የቤት ውስጥ ጥቃት ምላሽ እንዲሰጡ ማሰልጠን - የፕሮግራሙ ዐቢይ ማጠቃለያ

ጸሐፊ፡ ዶ/ር ሮሚና ኢስትራቲ  (Dr Romina Istratii)

ተርጓሚው: ዶ/ር ሃይለ ገዛኢ (Dr Haile Gezae)

ሰኔ 2014

የካቲት 2014 ፕሮጀክት dldl/ድልድል በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ካህናት ጋር ጣልቃ በመግባት ካህናቱ በማኅበረሰባቸው ውስጥ ለሚደርሰው የቤት ውስጥ ጥቃት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የካህናት ዝግጁነት ለመገንባት ጀመረ። ጣልቃ ገብነቱ የተነደፈው ዶ/ር ሮሚና ኢስትራቲ ቀደም ሲል በሰሜናዊ ኢትዮጵያ በትዳር አጋሮች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በሚመለከት ባደረጉት የረዥም ጊዜ የስነሰብእ(አንትሮፖሎጂ) ጥናት ላይ መሰረት ያደረገ ሲሆን፣ ይህም የሃይማኖት ቋንቋ መስፋፋቱን የሚያሳየው ካህናት እና ምእመናን በገጠር እና በከተማ ማህበረሰብ ውስጥ የቤት ውስጥ ጥቃቶችን እንዴት እንዳጋጠሙ እና ምላሽ እንደሚሰጡ እና ካህናት ስለ ጋብቻ የሚሠጡት ትምህርት እና በጥንዶች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን እና ጥቃቶችን በማስታረቅ ረገድ ያላቸው ወሳኝ የማስተማር ሚና ያሳያል።

ከጥናቱ ምልከታዎች እና ግኝቶች በመነሳት የቀጣዩን ጣልቃገብነት መርሃ ግብር በመንደፍ በተከታታይ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ዐውደ ጥናት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚያው ክልል ከሚገኙት የሃይማኖት አባቶች ጋር በማኅበረሰባቸው ውስጥ ስለየቤት ውስጥ ጥቃትንና ውጤታማ በሆነ መንገድ ግንዛቤአቸውን ለማሻሻል እና በተሻለ መንገድ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሥነ መለኮታዊ ዝግጁነታቸውን ለማጎልበት ያቀደው ነው። ይሁን እንጂ በጥቅምት 2012 ዓ.ም በትግራይ ክልል የተቀሰቀሰው ጦርነት ጣልቃ ገብነቱን ወደ ሌላ ጦርነት ወደ ሌለባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎችን ማዛወር አስፈልጓል። በመቀጠልም ምንም እንኳን የተለየ ባህላዊ ሁኔታ ቢኖርም ፣ በጋብቻ ውስጥ የሃይማኖት መለኪያዎች አስፈላጊነት እና ተፅእኖ እና የካህናት እና የቤት ውስጥ ጥቃት ልምድ ተመሳሳይ እንደሚሆን በመገመት ብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ሚኖሩበት ወደ ኢትዮጵያ የአማራ ክልል እንዲዛወር ተወስኗል። ይህንን ማላመድ በጊዜ ሂደት ለማሳካት በዐውደ ጥናቱ ዲዛይንና አቅርቦት ላይ ይዘቱን ከአካባቢው ባህላዊ ዐውድ ጋር ለማስማማት ጥረት ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና የማኅበረ ቅዱሳን ተራድኦ ኮሚሽን ከካህናት ማሰልጠኛ ማዕከላትና ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤቶች ጋር የሥራ ግንኙነት በመመሥረት እና አቅርቦቱ በመላው ኢትዮጵያ እነዚህን ዐውደ ጥናት ለማዳረስ ምቹ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ተረጋግጧል። ትብብሩ ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚህ ጣልቃገብነት ልማትና አተገባበር ላይ ተሳታፊ እንድትሆን በማድረግ የምርምርና አቅርቦት ቡድኑን የነገረ መለኮት እውቀት የጣልቃ ገብነት ትምህርቶች እና ውጤቶች እንዲያገኝና የቤተ ክህነት ድጋፍ በማድረግ ከካህናትና ምእመናን ጋር የሚደረገውን ጣልቃ ገብነትና ግንኙነት በማጎልበት እንዲሁም በቀጥታ ተጠቃሚ እንድትሆን አድርጓል። የዐውደ ጥናቱ የይዘት ዝግጅትና አቀራረብም)፣ የቤት ውስጥ ጥቃትን የተመለከቱ ሕጎች እንዲወጡ እና ማህበረሰብ አቀፍ ይግባኝ ስርዓቶችን በማዘጋጀት የሀገር ውስጥ ድጋፍ በሀገሪቱ ውስጥ የጥቃት ሰለባዎች እና የተረፉ በመርዳት ግንባር ቀደም በመሆን የሚሰራው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር(EWLA)ተገምግሞ ድጋፍ አግኝቷል፡፡

ከኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ጋር ባደረገው ሰፊ ምክክር እና ሰፊ ውይይት ከየሰሜን ሸዋ መንግስት ትብብር ከተረጋገጠ በኋላ ከደብረ ብርሃንና አካባቢው የተውጣጡ 155 የሃይማኖት አባቶችን ያሳተፈ ተከታታይ 7 ዐውደ ጥናቶች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል። የተከታታይ የሙከራ አቅርቦት በአራት ተከታታይ መነቃቅያ ስልጠናዎች ከመጀመሪያዎቹ 155 የሰለጠኑ የሀይማኖት አባቶች ጋር በተገናኘ 4 ተከታታይ 'የማደስ" ስልጠናዎች ተካሂደዋል ፤ የሃይማኖት አባቶች ቀጣይ የሆነ ድጋፍ እና ማበረታታት እና ያስፈልጋቸዋል በተባላው መሰረት በአርሶ አደር ተግባራቸው ውስጥ የተነሱ ጥያቄዎች ለመመለስና ቁሶቹ ለማስታወስ ተሞክሯል፡፡ የ “ማነቃቂያ” ስልጠናዎቹም በሙከራ ስልጠና ከተሳተፉ ከበርካታ ወራት በኋላ የተሳታፊዎችን አስተያየት ለማግኘት እና የፕሮግራሙ የሙከራ ምዕራፍ ካለቀ በኋላ የሙከራ ስልጠናው አዎንታዊ ዉጤቶችን እንዴት መቀጠል እንዳለበት አስተያየቶቻቸውን ለመሰብሰብ እንደ መድረክ ተጠቅመዋል።

ዐውደ ጥናቱ ለባህል ተስማሚ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን በዶ/ር ሮሚና ኢስትራቲይ በሁለት አሰልጣኞች፣ የሥነ ልቦና ባለሙያ እና በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ዲያቆን የሆኑት አቶ ሄኖክ ኃይሉ እና ከEWLA ጋር የሚሰሩት ጠበቃ ወይዘሮ ቤዛዊት ብርሃኑ ታግዘው በአማርኛ ሰጥቷዋል። እያንዳንዱ ዐውደ ጥናት ተሳታፊዎቹን አድካሚ እንዳይሆን እና በይዘቱ

ላይ እንዲያሰላስሉ ጊዜ ለመስጠት ለሁለት ግማሽ ቀናት ተሰጥቷል። በእያንዳንዱ ዐውደ ጥናት ሀ) የቤት ውስጥ ጥቃት ትርጓሜዎች፣ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉ እውነታዎች እና አመለካከቶች፣ ለ) የቤተክርስቲያን ትምህርት እና ከጋብቻ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ አባታዊ ምላሾችን የሚያካትት የስነ መለኮት ስልጠና እና ሐ) በሀገሪቱ የቤት ውስጥ ጥቃት ሕጎች ላይ ስልጠና እና ትምህርትን በመጠበቅ ላይ ያተኮሩ ገለጻዎች ነበሩ። ሁለተኛው ክፍል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጾታ ግንኙነት፣ በጋብቻ፣ በትዳር አብሮ መኖር እና የቤት ውስጥ ጥቃት በተመለከተ ያስተማረውን ትምህርት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ማኅበረ ቅዱሳን ተካቷል። ሦስተኛው ክፍል በቤት ውስጥ ጥቃት ላይ ስላለው የሕግ ማዕቀፍ፣ በካህናቱ ዙሪያ የሚገኙ የይግባኝ ሥርዓቶች፣ መረጃዎችን እና ምክሮችን ስለመጠበቅ መረጃ ሰጥቷል። ሦስቱ ክፍሎች በዶ/ር ሮሚና ኢስትራቲ አዘጋጅነት ዶሴ መልክ ተጠቃልለው በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን በነገረ መለኮትና የሕግ ሊቃውንቶች እና በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሥነ መለኮት ኮሌጆች፣ EOC DICAC እና EWLA አስተያየትና ግምገማ ቀርበዋል።

በቅርጸት ረገድ፣ ገለጻዎቹ ካህናቱ በሕብረተሰቡ ውስጥ ስላለው የቤት ውስጥ ጥቃት ውስብስብነት የበለጠ እንዲያውቁ ለመርዳት በንግግር እና የሁለቱኑም ሀሳቦች በሚያንፀባርቁ አቀራረቦች የተቀራረጡ ነበሩ። በተጨማሪ በቤተክርስቲያን የሚመሩ ከላይ ወደ ታች የሚዳረሱ ብዙ ሥልጠናዎችን በማሟላት ልምድ የሚለዋወጡበት መድረክ ለመፍጠር ጭምርም ነው። በተጨማሪም ዐውደ ጥናቶቹ ከተሳታፊዎች በቀጥታ ሐሳቦቻቸውን በመሰብሰብ የምርምር ዓላማዎችን ለማገልገል ያለመ ሲሆን ይህም በጊዜ ሂዴት የዐውደ ጥናቱ ይዘት ለማሻሻል እንዲሁም ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር ያለውን ቁርኝት ለማሳደግ ያለመ ነው።

እያንዳንዱ ዐውደ ጥናት ለተሳታፊዎች የምዘና መጠይቆችን በማደል የተጠናቀቀ ሲሆን የዐውደ ጥናቱ ቅርፅና ይዘት ለመገምገም የሚስችሉ ሰባት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ተደርጓል። የተሳታፊዎቹ ምላሾች እጅግ በጣም አወንታዊ ነበሩ። በተጨማሪማ በዐውደ ጥናቱ ይዘት እና በተካተቱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አጠቃላይ እርካታ ገለፁ።

በተለይም ተሳታፊዎች፦

- “ዘመናዊ” ወይም “ሳይንሳዊ” ዘዴ ከቤተክርስቲያን ነገረ መለኮት እና መንፈሳዊ ሥራ ጋር ማገናኘት የሚያስችል ብለው የገለጹትን አድንቀው፣ የዐውደ ጥናቱ ይዘት እና ቅርፅ በርዕሱ ላይ እውቀትን ለማስቀጠልና ካህናቱ ቀደም ሲል ከለመዱት ባህላዊ የሥልጠና ዓይነቶች ጋር በማነፃፀር በአዎንታዊ መልኩ አርአያ ሊሆን እንደሚችል በማመን በነሱ ላይ በስፋት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።
- ዐውደ ጥናቱ አላማውን በውጤታማነት እንዳሳካ ታሳቢ በማድረግ ስልጠናው በመደበኛነት እንዲቀጥል እና በአካል የመሳተፍ እድል ላላገኙ የሃይማኖት አባቶች እንዲደርስ ያለውን ፍላጎት ገልጿል።
- የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የጋብቻ ትምህርትና ምክሮች እንዴት ጠቃሚ ሁኖ እንዳገኙት እና ይህ እውቀት በማሕበረሰባቸው ውስጥ ከጋብቻ ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የተሻለ ምላሽ እንዲሰጡ እንዳደረጋቸው ተመልክቷል።
- በትዳር ጉዳዮች፣ በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት/ አለመሆንን እና በሕብረተሰቡ ላይ የሚደርሱ የቤት ውስጥ ጥቃት ዓይነቶች፣ በሀገሪቱ የሕግ ማዕቀፍ ላይ ያገኙትን መመሪያ፣ የምክር እና የይግባኝ አገልግሎቶችን በተመለከተ የተሰጡትን አቅጣጫዎች በተመለከተ የቀረበውን ገለጻ አድንቀዋል።
- መጽሐፍ ቅዱስን በማጣቀስ እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው፣ ሕጋዊ/ዓለማዊ እና ሥነ-መለኮታዊ አመለካከትን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል፣ እና በዐውደ ጥናቱ ላይ ያገኙዋቸውን አዳዲስ ቴክኒኮች በመጠቀም እንዴት ግጭቶችን እና የትዳር ጉዳዮችን መፍታት እንደሚችሉ ተግባራዊ በሆነ መልኩ እንደረዳቸው ይታመናል፡፡
- ለሥነ-መለኮታዊ ትምህርት እንደ ቀጥተኛ ማጣቀሻዎችን ባካተቱ እንደ ቋሚ ምንጭ በተሰጣቸው ዶሴዎች ምክንያት የበለጠ ዝግጁ እንደ ሆኑ ተሰማኝ።

- የዐውደ ጥናቱ ይዘት ለትዳር አጋሮቻቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እና ለመንፈሳዊ ልጆቻቸው ለማስተማር ያላቸውን ጠንካራ ፍላጎት እና ዝግጁነት ገልጸው፤ እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት ከክህነት ስልጣናቸው የሚጠበቀውን ባለማሳካታቸው በመፍራት በቤት ውስጥ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በማስተማር እንደገና የግዴታ ስሜት እንዲሰማቸው አድርጓል።

ከአቅርቦት ቡድኑ ምልከታ አንፃር ስናየው፣ ዐውደ ጥናቶቹ በአጠቃላይ ተሳታፊዎችን በማሳተፍ ረገድ ውጤታማ ነበሩ፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ክፍሎች እንደጠቀሟቸው አረጋግጠዋል። በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የተካተቱት ልምምዶች እና የቡድን ተግባራት ዋነኛ የዐውደ ጥናቱ አካል ሁነው አገልግሏል፣ ምክንያቱም ተሳታፊዎች እርስ በራሳቸው የሚግባቡበት ፣ የራሳቸውን ሁኔታ የሚያንፀባርቁበት ፣የንፅፅር መነፅር ከምርምር ግኝቶች እና ከራሳቸው ዐውድ ጋር እና ለተቀሩት ተሳታፊዎች ለማቅረብ መልስ ለማዘጋጀት አብረው የሚተገበሩበት አካባቢ እና 'አስተማማኝ ቦታ' ስለፈጠሩ ከዐውደ ጥናቱ በጣም ውጤታማ ከሆኑ አካላት አንዱ ሆኖ አገልግሏል። መልመጃዎቹ ተሳታፊዎችን እርስ በርሳቸው እንዲነጋገሩ፣ ሐሳባቸውን እና ልምዳቸውን እንዲያጋሩ እና አቋማቸውን ከሌሎች የሃይማኖት አባቶች ጋር እንዲነጋገሩ ለማበረታታት ጠቃሚ ነበሩ።

በማሻሻያ ስልጠና ጊዜ የተሰበሰቡ አስተያየቶች እንደሚያመላክቱት ከበርካታ ወራት በኋላ በሙከራ ዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡትን አወንታዊ ምላሽ ያረጋገጡ ሲሆን፣ የሙከራ ፕሮጀክቱ አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲቀጥል የጋራ ስምምነት የተደረሰ ሲሆን ነገር ግን ተደራሽነቱ ለማስፋት ወደ ብዙ የሃይማኖት አባቶች እንዲዳረስ እስከ መንደር ድረስ በመውረድ፣ ሌሎች ባለድርሻ አካላት፣ የሃይማኖት አባቶች ባለቤቶች፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ተሰሚነት ያላቸው እና የተከበሩ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ሴቶች እና ወጣት ያላገቡ ጥንዶች ከማግባታቸው በፊት እንዲዳረስ መሰራት እንዳለበት የጋራ መግባባት ላይ ደርሰዋል።

በዋናነት ደግሞ፡-

- ሁሉም አስተያየቶች አዎንታዊ የነበሩ ሲሆን፣ በተጨማሪ ደግሞ ሁሉም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙ እንዲቀጥል እና በሁለቱም ማለትም በይዘት እና ተደራሽነት እንዲስፋፋ ይፈልጋሉ።
- አንዳንድ የሀይማኖት አባቶች ፕሮጀክቱ የጋብቻን አስፈላጊነት ጠንቅቆ በመረዳት ችግሮቹን በሚገባ በመለየትና እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ተገቢውን አቀራረብ መስጠቱን ተገንዝቧል። ይህ አካሄድ በእውነት እና በተጨባጭ በሕብረተሰቡ ውስጥ ተጽእኖ ይኖረዋል ብለው አስበው ነበር፡፡
- ብዙዎች ሌሎች ካህናትን በተጨማሪ ለማሰልጠን ጥያቄአቸው አቅርበዋል፤ ይሁን እንጂ ይህንን ለማድረግ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል። አንድ ተሳታፊ የሰለጠኑትን የሀይማኖት አባቶች በገንዘብ በመደገፍ ካህናቱ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያከናወኗቸውን ስራዎችን እና ውጤቶቻቸውን በቀጣይነት እንዲያቀርቡ እና ለቀጣይ ስራቸው ማበረታቻ እንዲሆናቸው ማረጋገጥ እንደሚገባ ተናግረዋል።
- የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ለካህናት ሚስቶች፣ በአጠቃላይ በማሕበረሰብ ውስጥ ላሉ ሴቶች፣ ተደማጭነት ላላቸው ሽማግሌዎችና፣ ከጋብቻ በፊት ለወጣት ጥንዶችን ጨምሮ ለሌሎች ቡድኖች እንዲዳረስ ተሳታፊዎቹ ጠቁመዋል። አንድ ተሳታፊ ወንዶችን እና ሴቶችን በተለይም ጥንዶችን አንድ ላይ ማሰልጠን አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ይህም ለወንዶች ሳይናገሩ ሴቶችን ከሚያበረታቱ ድርጅታዊ ድርጊቶች እንዲወጡ ነው፤ ምክንያቱም ወንዶችን አለማሳተፍ ጉዳዩን ወደ ኋላ መመለስን ሊያስከትል ስለሚችል ነው፡፡
- አንዳንድ ካህናት ስለ ግላዊ ለውጦቻቸው በራሳቸው ግንዛቤ እና ባህሪ የተናገሩ ሲሆን፣ ሌሎችን ለማስተማር ያላቸው ቁርጠኝነትን እና ራስ እና ስለሌሎች ለመረዳት ኣዲስ ግንዛቤ እንደጨበጡ ይገልጻሉ።

ከግምገማ አካሄድ በመነሳት፣ የሚከተለውን ማለት ይቻላል፡-

- የግምገማ መጠይቆች በመጠቀም የተሳታፊዎች የስልጠናው ይዘት እና ቅርፅ (የዝግጅት አቀራረቦች እና የቡድን ተግባራት) ላይ የሰጡትን ፈጣን ምላሽ ለመገምገም የረዳ ሲሆን ለቀጣይ እና ለእውነተኛ/ተጨባጭ ጊዜ ትምህርት እና የአቅርቦት አቀራረብን ለማሻሻል አስችሏል።
- ሁለቱ የ'ማነቃቅያ' ስልጠናዎች በተሰጡበት ወቅት የተካሄዱት ውይይቶችም ሆኑ በመጨረሻ የተሰጡ አስተያየቶች፣ በሰለጠኑት የሃይማኖት አባቶች ቁልፍ የስልጠና መልእክቶችን ምን ያህል እንደተረዱ በደንብ ለመረዳት ያስቻለ ሲሆን ዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎችን እንዴት እንደጠቀማቸው ከራሳቸው ምስክርነት ለመስማት እድል ፈጥሮላቸዋል።
- ከተጠቀምነው የግምገማ አካሄድ የተማርነው ነገር ቢኖር፣ የፅሁፍ ምዘናዎች የተሣታፊዎችን አስተያየት ለመውሰድ ተገቢ ወይም ውጤታማ መንገድ አለመሆናቸውን ነው፤ ምክንያቱም አብዛኞቹ የሃይማኖት አባቶች ለመፃፍ ሆነ ሐሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለጽ እምብዛም አለመልመዳቸው ነው፡፡ በመጀመርያው ዙር ግምገማ ላይ ሐሳባቸውን በጽሁፍ ለመግለጽ ያልተመቻቸው የተለያዩ የሃይማኖት አባቶች እና ተሳታፊዎች ምላሾቻቸው ለመስጠትና የሰጡትን ምላሽ ለመያዝ የተለያዩ የግምገማ አቀራረቦች እና ዘዴ/ቴክኒኮች ቁልፍ ሆኖው ተገኝቷል።

dldl

ድልድል